# የቲቶ መልዕክት (10)

## ለቲቶ ጥናት የሚሆን መግቢያ

1ኛ ጢሞቲዎስ፥ 2ኛ ጢሞቲዎስ እና የቲቶ መልዕክቶች በአንድነት ፓስቶራል ኢፒስልስ (Pastoral Epistles) በመባል ይታወቃሉ። ይህ ስያሜ የተሰጣቸው በ18ኛው ምዕተ ዓለም ሲሆን ይህ ስያሜ በሰፊው የተለመደ ይሁን እንጂ ግማሽ እውነት ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው።

ጳውሎስ ይህንን መልዕክት በሚጽፍበት ወቅት ቲቶ ቀርጤስ በምትባለው ደሴት ላይ እንደነበረ ይታወቃል። በዚህ ስፍራ የምትገኘውን ቤተ ክርስትያን ጳውሎስ እንደመሰረታት የምናየው ነገር ባይኖርም ቲቶን ይዞ እንደሄደና መስመር የያዘ ጉባኤ እንዲመሰረት እንዳደረገ እናነባለን። መልዕክቱ የተጻፈበትን ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ከመጀመሪያ እስራቱ ተፈትቶ ግን ለሁለተኛ ጊዜ እስር ቤት ከመግባቱ ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ እንደሆነ ይናገራሉ። ይህም ማለት ጳውሎስ የሞተው ወደ 64 ዓ.ም እንደሆነ በመገንዘብ የተፃፈበትን ጊዜ ወደ 63 ዓ.ም ገደማ ያስቀምጡታል።

ይህች በሜደትራንያን የምትገኘው ደሴት ከመልዕክቱ እንደምናነበው በመጥፎ ባህርይና በውሸት የተካኑ ሰዎች የሞሉባት እንደነበረች ማየት ይቻላል (ቲቶ 1፥12-13) እንዲያውም በዚያን ዘመን "እንደ ቀርጤስ ሰው አትሁን" የሚል አባባል እንደነበረና ይህም ማለት "ውሸታም አትሁን" ከማለት እንደሚቀጠር ይናገራሉ። በቅድስናና በመልካም ሥራ ላይ ያተኮረ መልዕክት ካስፈለገበት ምክንያት ይህ ዋነኛው እንደሚሆን አያጠራጥርም።

ምንም እንኳን የቲቶ ስም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ተጠቅሶ ባይገኝም ሐዋርያው በጻፋቸው መልዕክቶች ውስጥ ወደ አስራ ሶስት ጊዜ ስሙ መጠቀሱ ጳውሎስ ከነበሩት የቅርብ ረዳቶች መሐል እጅግ የታመነና የተመሰከረለት አገልጋይ እንደነበረ ግልጽ ያደርግልናል። ሐዋርያው ለቲቶ ትልቅ አክብሮት እንደነበረውም ከ2ኛ ቆሮ 2፥12-14, 7፥5-7 እንረዳለን። ቲቶን ለመጨረሻ ጊዜ የምናየው በ2ኛ ጢሞ 4፥10 ላይ ሲሆን ይህም ምናልባት በቀርጤስ የነበረውን ትልዕኮውን ከፈጸመ በኋላ ሌላ ተልዕኮ በደልማጢያ ተቀብሎ እንደሚሆን ይገመታል። ቲቶና ጳውሎስ በቲቶ መልዕክት 3፥12 ላይ ባደረጉት እቅድ መሰረት በኒቆጵልዮን ተገናኝተው እንደሆነ ግን የሚታወቅ ነገር የለንም።

በተለያዩ ጊዜያት ቲቶ በቆሮንቶስ ከነጳውሎስ ጋራ በተያያዘ ሁኔታ እናየዋለን (2ቆሮ 2፥12-13, 7፥5-7, 7፥13-15, 8፥6, 8፥16-24) ይህም እውነት ቲቶ ከእነ ሉቃስና ጳውሎስ ጋራ አብሮ በአገልግሎት ላይ ተሰማርቶ እንደነበረ ጥሩ ፍንጭ ይሰጠናል።

በቲቶ 1፥5 እንደምናነበው በቀርጤስ የመሆኑ ዋነኛ ምክንያት ቤተ ክርስያን በዘፈቀደ ወይም እንደተመቸ የምትሄድ ሳትሆን ሥርዓት ይዛ በተደራጀ ሁኔታ መመራቷ አስፈላጊ ስለሆነ በዚያ ሁኔታ እንዲያደራጅ ሐዋርያው እንደራሱ አድርጎ የወከለው እንደሆነ እናያለን።

# ጥናት አንድ (ቲቶ 1፥1-9)

*የጥናት አላማ፡ ሽማግሌ፥ እረኛ፥ ኤጲስ ቆጶስና፥ ጳጳስ ሁሉም አንድን ሃሳብ የሚገልጡ እንደሆኑ ለማስተማርና እንዲሁም ከሌሎች ባህርያት በተጨማሪ የእግዚአብሄር ቃል መብሰልን እንደሚጠይቅ ለማሳየት።*

የምናሰላስለው ጥቅስ፦ ‹‹ሌሎችን ትክክል በሆነው ትምህርት እንዲያበረታታና ይህንኑ ትምህርት የሚቃወሙትን ይወቅስ ዘንድ እንደተማረው በታመነ ቃል የሚጸና መሆን አለበት፡፡›› ቲቶ 1:9

1. ጳውሎስ ስለራሱ ማንነትና ጥሪ በቁ 1-4 ውስጥ የሚናገራቸውን ሃሳቦች በዝርዝር ተናገር።
2. ሐዋርያው ጳውሎስና ቲቶ በቀርጤስ አብረው እንደነበሩ የሚያመለክተን ክፊል የትኛው ነው? 1፥5ና 3፥12ትን በማገናዘብ ስትመለከት ስለቲቶ ተልዕኮ ምን ትረዳለህ?
3. ቲቶ የቀርጤስ ቤተ ክርስትያን እረኛ እንደሆነ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች እንዳሉ ይታወቃል። በጥያቄ 2 ላይ የሰፈሩት ሁለት ጥቅሶችና እንዲሁም "በየከተማው" የሚለው ሃሳብ ከዚህ አይነቱ አመለካከት ጋራ ይስማማሉ ብለህ ታምናለህ ወይ? ምክንያትህን አስረዳ።
4. በእግዚአብሄር ሕዝብ ላይ ሊሾሙ ያላቸው ሽማግሌዎች ጳውሎስ ራሱን "ባሪያና... ሐዋርያ" በማለት ያስተዋወቀበትን ሃሳብ መረዳት ለሚጠብቃቸው አገልግሎት የሚጠቅማቸው ይመስልሃል ወይ? አስረዳ።
5. የቤተ ክርስትያን መሪዎችን ለመጥቀስ በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ (ቲቶ 1፥5, ቲቶ 1፥7, 1ኛ ጢሞ 3፥1-2, ሐዋ 20፥28, 1ኛ ጴጥ 5፥1-4) የተጠቀሱትን መጠሪያ ስሞች ዘርዝር።
6. ከላይ የተዘረዘሩት መጠሪያዎች በኤፌሶን 4፥11 እረኞች (ፓስተሮች) ከሚለው መጠሪያ ጋራ የምታየው አንድነት ወይም ልይነት ምንድነው? ለምን ይህን ልትል ቻልክ?
7. ከቁ 7-9 ለሽማግሌነት የሚያበቁት ዝርዝር መመሪያዎች ሰፍረዋል። በተለይ ከእግዚአብሄር ቃል እውቀት አንጻር ሊኖረው ስለሚገባው እውቀት የተነገረው ሃሳብ የትኛው ነው? ከዚህ አንጻር የሚጠበቁበት ሁለት ችሎታዎች ምንና ምንድናቸው?
8. 1ጢሞ 3፥2 "ለማስተማር የሚበቃ" የሚለውንና ቲቶ 1፥9 "ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅስ ይችል ዘንድ.." የሚሉትን ሃሳቦች ከተመለከትክ በኋላ ሽማግሌ የማስተማር ችሎታ ሊኖረው ይገባል ሲል ምን ትረዳለህ?
9. የቤተ ክርስትያን ሽማግሌ/ፓስተር/ኤጲስ ቆጶስ/ጳጳስ ለመሆን ተመኝተህ ታውቃለህ ወይ? ከሆነ በ1ኛ ጢሞ 3፥1 መሰረት መልካም ተመንተሃል። ለዚያ የሚያበቃህን ባህርይ ለመገንባት ሕይወትህን በዚህ መሰረት አዘጋጅ።

# <u>ጥናት ሁለት (ቲቶ 1፥10-16)</u>

*የጥናቱ ዓላማ፣ የቤተ ክርስትያን መሪ የመምከርና የማጽናናት ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን በብርቱ የመውቀስም ነገር ስለሚጠበቅበት በጸሎት መርዳት የምዕመናን ሁሉ ሃላፊነት እንደሆነ ለማሳሰብ።*

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹ስለዚህ አጥብቀህ ገስጻቸው፤ይኸውም ትክክለኛ እምነት እንዲኖራቸውና የአይሁድን ተረት ወይም ከእውነት የራቁትን ሰዎች ትዕዛዝ እንዳያደምጡ ነው፡፡›› ቲቶ 1:13-14

1. ቲቶ 1፥10-16 በአንድነት ይነበብ። በቁ 10-11 መሰረት ሐዋርያው በቀርጤስ ስለሚገኙ ሰዎች ስለ ሀ) ዓይነትታቸው ለ) ማንነታቸው ሐ) አድራጎታቸው መ) የሚያደርሱት ጥፋት ምን ይላል?
2. ከላይ በተዘረዘሩት ዓይነት ሰዎች ላይ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ጳውሎስ ምን ይላል?
3. በቁ 11 ላይ "የማይገባውን እያስተማሩ.." በሚለውና በቁ 9 ለሽማግሌዎች መመዘኛ ተሰጠውን ሃሳብ በማነፃጸር አስረዳ።
4. "..በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው።" ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል? ተወቃሹስ ማን እንደሆነ ታስባለህ?
5. "ይልቁንም ከተገረዙት ወገን" ስለነዚህ ሰዎች ቃልና ተግባር ይህ ክፍል በግልጽ የሚናገረው ነገር ምንድነው?
6. እግዚአብሄርን አውቃለሁ እያሉ አፀያፊ ሥራን መስራትን የሚለማመዱ ሰዎች በዚህ ዘመንስ ይኖራሉ ወይ? እነዚህን ለሚመስሉ ሰዎች የቤተ ክርስትያን መሪዎች ሃላፊነት ምን ይመስልሃል?
7. እግዚአብሄርን እናውቃለን ማለት ብቻ በቂ አለመሆኑን የሚያስተምረን ክፍል የትኛው ይመስልሃል? እግዚአብሄርን ከሚያውቅ ሰው ስለሚጠበቅበት ነገርስ ይህ ክፍል ምን ያስተምረናል?
8. "አፋቸውን መዝጋት ይገባል።" "በብርቱ ውቀሳቸው" የሚሉትን ስታይ ስለ ሽምግልና አገልግሎት ምን ይጠቁምሃል?
9. ሽማግሌዎች ከሰዎች ጋራ በለስላሳ ቃል ብቻ የሚመክሩ እንዳልሆኑ በመረዳት ጌታ ይህንንም እውነት ለመታዘዝና ለመፈጸም እንዲችሉ ጸጋ እንዲያበዛላቸው በጸሎትህ ዘወትር አስባቸው።

# ጥናት ሶስት (ቲቶ 2፥1-10)

የጥናቱ ዓላማ፥ በማንኛውም የእድሜ ክልል ብንገኝ የእግዚአብሄር አገልጋይ የሆነ ሰው ቢመክረንና ሊያርመን ቢነሳ ከጌታ የተቀበለው ሃላፊነት እንደሆነ አውቀን በትህትና ለመቀበል ራሳችንን ለማዘጋጀት።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡-‹‹አረጋውያን ጭምቶች፤ የተከበሩ፤ ራሳቸውን የሚገዙና በእምነት፤ በፍቅርና በትዕግሥት ጤናማነት ያላቸው እንዲሆኑ ምከራቸው፡፡›› ቲቶ 2፡2

1. ምዕራፍ ሁለትን ሲጀምር "አንተ ግን" የሚለው አጀማመር ምን የሚጠቁመን ነገር ይኖራል ብለህ ታስባልህ? ሊያያይዘው ያሰበውስ ከየትኛው ሃሳብ ጋራ ነው?
2. "ሽማግሌዎች" "አሮጊቶች" "ቆነጃጅት" "ጎበዞች" "ባሪያዎች" የሚሉትን ዓይነት ቃላት ስታነብ ስለ ቤተ ክርስትያን ምን የሚያስረዳህ ነገር አለ?
3. ሽማግሌዎች፥ ቆነጃጅትን፥ ጎበዞችንና እንዲሁም አሮጊቶችን በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲመክር የተጠየቀው አንድ የጋራ ነገር ተጠቅሶ ይገኛል። ይህ ቃል ምን እንደሆነ ተናገር። ይህስ ስለዚህ ነገር አስፈላጊነት ምን ይጠቁማል?
4. "የማይገባውን እያስተማሩ ቤቶችን በሞላው ስለሚገለባብጡ.." ይላል ለቲቶ ደግሞ "የሚገባውን ተናገር።" በማለት በቤተሰብ ለሚገኙት ሁሉ የሚያስተምረውን ይመክራል። ሁለቱን ሃሳቦች በማነጻጸር ምን ትማራለህ?
5. በ2፥2, 5, 7, እና 10 ላይ "ምከራቸው" የሚሉትን ቃላት እናገኛለን። ይህ አባባልና በሌሎች ክፍሎች ውቀስ፤ ገስጽ፥ ከሚሉት ሃሳቦች ጋራ የሚቃረን ይመስልሃል ወይ? ይህስ የእግዚ አብሄር አገልጋይ መውሰድ ስለሚገባው እርምጃዎች ምን ያስተምርሃል?
6. በቁ 7-8 ስለ ቲቶ ቃልና ተግባር ምን የሚነግረን ነገር አለ? ይህንንስ በ 1፥16 ከተነገረው ሃሳብ ጋራ እንዴት ታገናዝበዋለህ?
7. ቁ 4 "የእግዚአብሄር ቃል እንዳይሰደብ" ቁ 7 "ስለ እኛ የሚናገረውን መጥፎ ነገር ሲያጣ እንዲያፍር" ቁ 9 "ስለ እግዚአብሄር የሚሆነውን ትምህርት በሁሉ ያስመሰግኑ ዘንድ" እነዚህንና የመሳሰሉትን ስታነብ የምትማረው ነገር ምንድነው?
8. የእግዚአብሄር አገልጋይ ተልዕኮውን ለመወጣት እንዲቀለው ልታደርግለት የምትችለው መንገድ ይኖራል ወይ? ወደፊት ምክርንም ሆነ ተግሳጽን ለመቀበል ልብህን ዝግጁ አድርግ።

# <u>ጥናት አራት (ቲቶ 2፥11-15)</u>

***የጥናት ዓላማ፣ የእግዚአብሄር ጸጋ ሰዎችን ከማጽደቅ አልፎ የተቀደሰ ሕይወትን እንዲኖሩ የአማኞች አስተማሪ እንደሆነ ለመማር።***

የምናሰላስለው ጥቅስ፦‹‹ይህም ጸጋ በሃጥያት መኖርንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛት፤ በጽድቅና በእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት እንድንኖር ያስተምረናል።›› ቲቶ 2፡12

1. 2፥2-10 ሽማግሌዎች፤ አሮጊቶች፤ ቆነጃጅት፤ ጎበዞች፤ ባሪያዎች ተብለው የተዘረዘሩት ሃሳቦች ከታች በቁ 11-14 ከተጠቀሰው የእግዚአብሄር ጸጋ መገለጥ ጋራ እንዴት ይያያዛሉ?
2. የእግዚአብሄር ጸጋ የሚያስተምረንን ነገሮች ሁሉ በመዘርዘር ተናገር። 2፥11-14
3. ዓለማዊ ምኞትን መካድ ስለሚለው ሃሳብ የምትረዳው ነገር ምንድነው?
4. በነዚህ ቁጥሮች አማካኝነት የጌታን መምጣት መጠባበቅ በአኗኗራችን ላይ ሊያስከትል ስለሚገባው ነገር ምን ታያለህ?
5. የጌታችንን መገለጥ በዚህ ክፍል ምን ብሎ ነው የሚጠራው? ይህ ክፍል ኢየሱስን የሚይስተዋውቅባቸውን አምስት ስሞች ተናገር።
6. "በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል" ከሚለው ሐሳብ ምን ትረዳለህ?
7. ቁ 14 "ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቷል" በማለት ነፍሱን ስለሰጠበት ምክንያት የሚጠቅሳቸው ሁለት ሃሳቦች ምንና ምንድናቸው? እነዚህስ ሃሳቦች የእግዚ አብሄር ጸጋ ያስተምረናል ከሚለው ሃሳብ ጋራ እንዴት ታገናዝባቸዋለህ?
8. "ይህንን በሙሉ ስልጣን ተናገር.." ከሚለው አባባል ምን ትረዳለህ? ጢሞቲዎስ መናገር የሚጠበቅበትስ ለነማን ይመስልሃል?
9. ዛሬ ስለ እግዚአብሄር ጸጋ የተማርከውና በውስጥህ የቀረልህን አንድ ነገር ለወገኖች በአጭሩ አካፍል።

# ጥናት አምስት (ቲቶ 3፥1-7)

**የጥናቱ ዓላማ፣ አማኝ በእግዚአብሄር ጸጋ ከጸደቀና መንፈስ ቅዱስ ውስጡ ከገባ በኋላ እንደ ቀድሞው ዓይነት ህይወት መኖር መቀጠል እንደማይገባው ለመማር።**

የምናሰላስለው ጥቅስ፦‹‹ቀደም ሲል እኛ ራሳችን ማስተዋል የጎደለን፤ የማንታዘዝ፤ የተታለልን፤ የተለያየ ምኞትና ምቾት ባሪያ ሆነን…በምቀኝነት እንኖር ነበረ፡፡›› ቲቶ 3፡3

1. በም 2፥11-14 የጸጋውን ሥራ ከነገረ በኋላ በምዕራፍ ሶስት የመጀመሪያ ቁጥሮች ላይ በግል ህይወታቸው እንዲታይ የሚናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር።
2. በቁ 1 ላይ "ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጁ.." ሲል የምትረዳው ነገር ምንድነው?
3. በቁ 1-2 ከተዘረዘሩት ነገሮች ለክርስትያኖች ይበልጥ ትግል የሚሆንባቸውና በህይወታቸው ለመተርጎም የሚቸገሩበት የትኛው ይመስልሃል?
4. ቁጥር ሶስትን በማንበብ ስለ ቀደመው ህይወታችን ምንነት ምን ታያለህ? "እኛ ደግሞ አስቀድመን" የሚለው ሃሳብስ ስለ ዛሬ የሚነግርህ ነገር ምንድነው?
5. ለምን ይመስልሃል በዚህ ሥፍራ ስለ እኛ የቀድሞ ህይወት ምንነት መናገር ያስፈለገው?
6. ምዕራፍ 3፥4-7 ትን በማንበብ እግዚአብሄር ስላደረገልህ ነገሮች የምታያቸውን በሙሉ ዘርዝር። በዚህ ውስጥ ስለ አንተ አስተዋጽዖ ምን ይላል?
7. በ3፥6 የምናየው የጸጋ ሥራና በ 2፥11-13 የምናየው የጸጋ ሥራ ልዩነት ምንድነው? በእነዚህስ መሃል ቅራኔ ይታይሃል ወይ? አስረዳ።
8. በ3፥6-7 ላይ ጸገው በእኛ ላይ ስለ ፈሰሰበት ምክንያት ምን ይላል? ይህስ የሆነው በማን በኩል ነው?
9. የቀደመውን ህይወትህን ታስታውሰዋለህ ወይ? ካሬስ ከዚያ የተለየ ህይወት እየኖርክ ነው ወይ? መንፈስ ቅዱስ እንደ ህግ እንዴት እንደምንኖር ማስተማር ብቻ ሳይሆን የምንኖርበትን ሃይልም ስለሚሰጠን በእርሱ ሃይል መመላለስን ተለማመድ።

# ጥናት ስድስት (ቲቶ 3፥8-15)

የጥናት አላማ፡ የእግዚአብሄር ሰዎች የክርክር ሰዎች ሳይሆኑ በመልካም ሥራ የተመሰከረላቸው ፍሬአማ ሰዎች መሆን እንደሚጠበቅባቸው ለማሳየት።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡-‹‹ነገር ግን ከንቱ ከሆነ ክርክርና ከትውልድ ሐረግ ቆጠራ፤ ከጭቅጭቅና ስለህግ ከሚነሳ ጠብ ራቅ፡፡›› ቲቶ 3፡9

1. በቁጥር 8 ላይ መልካምን ሥራ ስለማድረግ አስፈላጊነት ሐዋርያው ጳውሎስ የሚሰጣቸው ሁለት ምክንያቶች ምንድናቸው?
2. በ 3፥5 ላይ "እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረ ሥራ አይደለም" በማለት የእኛ መልካም ሥራ እንዳላስፈለገ ይነግረናል። በቁ 8 ላይ ደግሞ "በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ" በማለት አስፈላጊነቱን ያረጋግጥልናል። ታዲያ እነዚህን ሁለት ሃሳቦች እንዴት ታስታርቃለህ?
3. መልካምን እንዲያደርጉ የሚገፋፋውን ያህል በአንፃሩ ጸሃፊው አማኞች እንዲርቁ የሚያዛቸው ነገሮች አሉ እነዚህ ምንድናቸው? ለዚህስ የሚሰጣቸው ሁለት ምክንያቶች ምንና ምንድናቸው?
4. "በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ" ቁ8, 14 የሚለውን ሃሳብ በመመልከት "እንዲጸኑ" የሚለው ቃል ምንን ይጠቁመናል? ከዚህ አባባል አንጻር መልካምን ሥራ መጀመር ነገር ግን አለመጽናት ሊኖር ይችላል ወይ? አስረዳ።
5. "በራሱ ላይ ፈርዶ ሃጥያትን እንዲያደርግ አውቀህ" የሚለው አባባል ስለዚህ ሰው የሚያስረዳህ ነገር ምንድነው? ለምን ይመስልሃል ቃሉ ይህንን ከሚመስሉ ሰዎች እንድንርቅ የሚያስጠነቅቀን?
6. "..በጉዞአቸው ተግተህ እርዳ" የሚለው ሃሳብ ቲቶ የእግዚ አብሄርን እውነት አስተላላፊ ብቻ ሳይሆን የተናገረውን እንዲኖር እንደሚጠበቅበት እናያለን። ከዚህ እውነት ለራስህ የምትማረው ነገር ምንድነው?
7. ቁጥር 14 "ከወገናችን ያሉት.." ሲል ስለነማን ነው የሚናገረው? በዚሁ ቁጥር ላይ ፍሬቢስነትንና መልካም ሥራን ጸሐፊው እንዴት ነው ያያያዘው?
8. መልካም ሥራና ደህንነት ያላቸውን ግንኙነት የተረዳኸውን አስረዳ። ስለዚህ በጸጋ ስለመዳንህ ጌታን እያመሰገንክ መልካሙን ሥራ ደግሞ ለመሥራት በጌታ ጸጋ በርታ።